የመጽሐፍ ግብዣ

□

- ርእስ፦ ፍኖት መንፈሳዊት (The Way of a Pilgrim)

- ትርጕም፦ ክብረ ሃይማኖት የትርጕም ማኅበር።

- የታተመበት ጊዜ፦ ቀዳሚ ዕትም፥ ፳፻፲ወ፯ (2017) ዐ.ም፤

ኹለተኛ ዕትም፥ ነሐሴ ፳፻፲ወ፰ (2018) ዐ.ም።

- ገጽ፦ መቅድምና መግቢያን ሳይጨምር ፪፻፶፰ (258) ገጾች አሉት።

- መጠን፦ A5

- የታተመውና የተዘጋጀው፦ ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

- አሳታሚና አከፋፋይ፦ አርጋኖን መጻሕፍት መደብር።

እንግባ ...

‘ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፥’

‘እኔ ኀጢአተኛውን ማረኝ!’

“ያለ ማቋረጥ ጸልዩ” (፩ተሰ ፭፥፲፯) የሚለውን ሐዋርያዊ ትእዛዝ፥ ቃሉን ለማንበብ ቀላል ቢሆንም፥ በተግባር ለመኖር ግን እጅግ ከቡድና ትዕግሥትን የሚጠይቅ መንፈሳዊ ተግባር ነው። ይህን አምላካዊ ቃል የሕይወቱ ማእከል ለማድረግ የናፈቀውና በዚህ መጽሐፍ ስሙ ያልተጠቀሰው መንፈሳዊ ተጓዥ፣ በመላው ሩሲያ ያደረገውን አስገራሚ የሕይወት ጕዞ በዚህ ድንቅ መጽሐፍ ያካፍለናል።

በደረቅ ዳቦ፣ በመጽሐፍ ቅዱስና በ«ፍሎካሊያ» (Philokalia) መጽሐፍ ብቻ ታጅቦ፣ ልቡናውን በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር በማቅናት የጀመረው ይህ ጕዞ፤ የጸሎተ ኢየሱስን (የልብ ጸሎትን) ገቢረ ኀይል በራሱ በተጓዡ ሕይወት ያስተምረናል።

“The Way of a Pilgrim” (ፍኖት መንፈሳዊት) ከተጻፈበት ከ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቈጠሩ ክርስቲያኖችን ልብ ሲማርክና ሕይወታቸውን ሲለውጥ የኖረ ግሩምና ማራኪ መጽሐፍ ነው። ዋንኛ ዐላማዉም **“አቤቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ማረኝ”** የሚለውን ዐጭርና ድንቅ ጸሎት በመደጋገም፣ ጸሎተ ከንፈርን ወደ ጸሎተ

ልብ እንዴት ማሳደግ እንደሚቻልና ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ ጥልቅ ኅብረት ማድረግን ማሳየት ነው። ይህ መጽሐፍ ተራ የታሪክ ትረካ ሳይሆን፥ እያንዳንዱ አንባቢ የራሱን መንፈሳዊ ጕዞ እንዲጀምር የሚነሣሣበት መንፈሳዊ ጥሪ ነው። አንድም፥ ከዓለም ጫጫታ ርቆ በልቡናው ማኅደር ውስጥ አምላኩን እንዴት ማግኘት እንደሚችል የሚያሳይ መመሪያ ነው። የዚህን ተጓዥ ፈለግ በመከተል፥ በማያቋርጥ ጸሎትና በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ የሚገኘውን እውነተኛ የነፍስ ሰላም ማግኘት ከፈለግን ጥሩ አብነት ነው። ጸሎት የሁሉ ነገር መልስ ማግኛ መንገድ ነውና! ተጓዡም የጕዞውን መነሻ ሲያስረዳ የነፍሱን ጥማት እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፦

“በየስፍራው የምንከራተተውም «ያለ ማቋረጥ ጸልዩ» የሚለውን የሐዋርያውን ትእዛዝ ጥልቅ ምስጢርና ትርጕም ለመረዳት በሚቃጠል ከፍተኛ ፍላጎትና ናፍቆት ተገፋፍቼ ነው። ይህን ለማወቅ ብዙ ቦታ ተመላለስሁ፤ ብዙ አስተማሪዎችንና ሊቃውንትንም ጠየቅሁ፤ ነገር ግን የነፍሴን ጥማት ሊቀርጥልኝ የሚችል አጥጋቢ ምላሽ አላገኘሁም። በመጨረሻም እግዚአብሔር መንገዴን አቅንቶልኝ፣ የማላቋርጠውን የልብ ጸሎት ምስጢር ወደሚያስተምረኝ አባት ዘንድ መራኝ...” ይለናል።

እኛም የንባብ ግብዣ ጕዟችንን ይዘቱን በመመልከት እንቃኝ ...

#የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፉ ስድስት መሠረታዊ ምዕራፎች ያሉት ሲሆን፥ በተጨማሪም የአባቶችን መመሪያ የያዘ ዐባሪን አካቷል።

- ምዕራፍ ፩ [፩ ትረካ]

ይህ ምዕራፍ መንገደኛው "ያለማቋረጥ ጸልዩ" የሚለውን ሐዋርያዊ ቃል በተግባር እንዴት መፈጸም እንደሚቻል ለመረዳት የሚያደርገውን ፍለጋ ያትታል። በዚህም ፍለጋው መንፈሳዊ መምህር (አረጋዊ አባት) በማግኘት ስለ "ጸሎተ ኢየሱስ" (Jesus Prayer) ይማራል፤ እንዲሁም "ፊሎካሊያ" (Philokalia) የተሰኘውን የቅዱሳን አበው መጽሐፍ አግኝቶ ጸሎቱን እዚያ ላይ ባለው ምክረ አበው መሠረት በነቢበ ከንፈር አሐዱ ብሎ ጸሎቱን መለማመድ ይጀምራል።

- ምዕራፍ ፪ [፪ ትረካ]

በመጀመሪያው የትረካ ምዕራፍ በነቢበ ከንፈር ይደረግ የነበረው ጸሎት፣ በዚህኛው ምዕራፍ ወደ ልብ ወርዶ "ጸሎተ ልብ" (Prayer of the Heart) ሆኖ በራሱ መንቀሳቀስ ሲጀምር እናያለን። ገቢረ ጸሎቱ ሥራው ይጀምራል። መንገደኛው በጕዞው ከባድ ፈተናዎች (መዘረፍና መደብደብ) ቢያጋጥሙትም፣ ከጸሎቱ የሚያገኘው አምላካዊ አጽናኝነት ችግሮቹን ሁሉ አስረስቶትና አስችሎት ጕዞውን ይቀጥላል። በተጨማሪም ቅዱስ ወንጌልን በማንበብ ከስካር ሕይወት ወጥቶ ኑሮና አጠቃላይ ሕይወቱ ተቀይሮ ስላዳነው መኰንን፣ በጥርጣሬ ስለሚፈተነው የደን ጠባቂ፣ እንዲሁም ስለ ጸሎት ጎይል ከተለያዩ ሰዎች ጋራ

የሚያደርጋቸውን መንፈሳዊ ገጠመኞች ያሳያል። እኔ በተለይ የምወደው ምዕራፍ ትረካ ነው። ቅዱስ ወንጌልን በማንበብ ሕይወታችንን እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል የመከሩኑ ምስክርነት ልብን ያሃሣል። ትክክልም ነው!

- ምዕራፍ ፫ [፫ ትረካ]

በዚህ ክፍል፣ መንገደኛው ወደ ኢየሩሳሌም ጕዞውን ከመጀመሩ በፊት በኢርኩትስክ ለሚገኘው መንፈሳዊ አባቱ የራሱን የሕይወት ታሪክ ወደኋላ ተመልሶ ይተርክላቸዋል። ታሪኩም ከልጅነት ሕይወቱ የሚጀምር ሲሆን፥ ወላጆቹን በሞት ካጣ በኋላ በአያቱ እንዳደገና መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንደተማረ ያስረዳል። ነገር ግን ከታላቅ ወንድሙ ጋራ የነበረው ግንኙነት ፈታኝ እንደነበር፣ ወንድሙ በአልኮል ሱሰኝነትና በቅናት ተገፋፍቶ ቤታቸውን በእሳት ማቃጠሉን መንገደኛውና ሚስቱ ሁሉንም ንብረታቸውን አጥተው ለከፍተኛ ችግር እንደተዳረጉ፣ በችግራቸው ጊዜም በጸሎትና በእምነት ጸንተው ዐዲስ ሕይወት ለመጀመር መሞከራቸውን፣ ከኹለት ዓመታት በኋላም ሚስቱ በድንገተኛ ሕመም ስትሞትበት በከባድ ሐዘን ውስጥ መግባቱን፣ ከዚህም ከባድ ሐዘንና ብቸኝነት የተነሣ፣ የቀረውን ጥቂት ንብረት ሽጦ መጽሐፍ ቅዱሱን ብቻ በመያዝ "ያለማቋረጥ መጸለይ" የሚለውን ምስጢር ለማግኘት መንፈሳዊ ጕዞውን (መንገደኝነቱን) እንደጀመረ ይገልጻል። ተጓዡ ምን ዐይነት ጠንካራና የውሃ ሰው እንደሆነ የምንተዋወቀው በዚህ ምዕራፍ ትረካ ነው።

- ምዕራፍ ፬ [፬ ትረካ]

ይህ ክፍል መንገደኛው ጸሎተ ኢየሱስን ("አቤቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ማረኝ" የሚለዉን) በልቡ ውስጥ በሚገባ አዋሕዶ የሚያደርገውን ቀጣይ ጕዞ ያሳያል። ወደ ኢየሩሳሌም ለማቅናት እቅድ ቢኖረውም በተለያዩ ያልተጠበቁ ክሥተቶች ጕዞው ይዘገያል፤ ይደናቀፋል። ነገር ግን ሁሉንም ኹኔታዎች በእግዚአብሔር ፈቃድና መግቦት አምኖ ይቀበላል። በጕዞው ላይም የተለያዩ ሰዎችን (ለምሳሌ ዐብሮት የሚጓዘን መስማት የተሳነው አዛውንት) ያገኛል፤ የጸሎትና የመንፈሳዊነት ልምዱንም ለሌሎች ያካፍላል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጸሎት ሕይወቱ ከከንፈር ንባብ አልፎ ወደ ልብ በመውረድ፣ ከእስትንፋሱ ጋራ የተዋሐደና ለነፍስ ዕረፍት የሚሰጥ ጸሎት ሆኖ እናገኘዋለን። ጸሎቱ አድጓል። በመንገዱ ላይ የተለያዩ ፈተናዎችና ውጣ ውረዶች (ለምሳሌ በዘራፊዎች መጠቃት) ቢገጥሙትም፣ በ"ፊሎካሊያ" (Philokalia) መጽሐፍ የአበው ትምህርትና በጸሎቱ ኀይል ውሳጣዊ ሰላሙን ሳይነጠቅ፣ ለፍጥረታት ሁሉ ፍቅርን እያዳበረ መንፈሳዊ ጕዞውን ይቀጥላል።

እዚህ ጋ የ"መንገደኛው ታሪክ" (The Way of a Pilgrim) የመጀመሪያው መጽሐፍ በአራት ትረካዎች የሚያበቃ ሲሆን፥ ዐምስተኛውና ስድስተኛው ትረካዎች (ምዕራፎች) "መንገደኛው ጕዞውን ይቀጥላል" (The Pilgrim Continues His Way) በሚል በሚታወቀውና በኋላ በተገኘው ኹለተኛው የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እነዚህ ክፍሎች ይበልጥ ሥነ-መለኮታዊ ተዋሥኦንና የጸሎትን ተግባራዊነት የሚያጐሉ ናቸው።

- ምዕራፍ ፭ [፭ ትረካ]

በዚህ ክፍል መንገደኛው ከእርሱ ጋራ ዐብሮ ከሚጓዝ አንድ ዐይነ ስዉር ጋራ ያሳለፈውን ጊዜ ይተርካል። ዐይነ ስዉሩን [ልበ ብርሃን] ሰው ጸሎተ ኢየሱስን ("ጸሎተ ልብ") እንዲጸልይ ያስተምረዋል፤ በዚህም ዐይነ ስዉሩ ሰው ሥጋዊ ዐይኑ ባያይም በጸሎቱ ኀይልና በእግዚአብሔር ጸጋ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ብርሃንን (ብርሃነ ልቡና) ሲያገኝ እናያለን።

- ምዕራፍ ፮ [፮ ትረካ]

ይህ ክፍል መንገደኛው ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች (ከዩኒቨርሲቲ ምሁር/ፕሮፌሰር፣ ከካህናትና ከሌሎችም ምእመናን) ጋራ ስለ ጸሎት፣ ስለ እምነት፣ ስለ ጸጋና ስለ ነጻ ፈቃድ የሚያደርጋቸውን ጥልቅ ሥነ-መለኮታዊ ተዋሥኦ (ውይይቶች) ያሳያል። ዋና መልእክቱም "ያለማቋረጥ መጸለይ" በገዳም ለሚኖሩ አበው ብቻ ሳይሆን፥ በዓለም ውስጥ በተለያዩ ተግባራት ለተሰማሩ ሰዎችም ሁሉ የሚቻልና የሚገባ መሆኑን ማስረዳት ነው።

#የግብዣ መውጫ

እውነተኛ ጸሎት የተወሰነ ሰዓት የሚደረግ የዘልማድ ድርጊት ሳይሆን፣ ከእስትንፋስ ጋራ የተዋሐደ የሕይወት ዘይቤ መሆኑን ይህ መጽሐፍ ያሳየናል። በዘመናችን ሁከት፣ ሩጫ፣ ውጥረትና መባከን በበዛበት በዚህ ጊዜ፣ መጽሐፉ ለምእመናን የጽሙናን፣ ቀለል ያለ ሕይወትንና ራስን የመግዛትን ዋጋ ያስተምራል። ከዚህም ባሻገር ማንም በቀላሉ ያላገኘውን፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ነፍስ የሚጠማውን የነፍስ ጸሎት የሆነውን ጸሎተ ኢየሱስን በየሰዓቱና በየኹኔታው እንድንጸልይ ያበረታታናል።

"ፍኖት መንፈሳዊት" ተብሎ የተተረጐመው ይህ ማራኪ መጽሐፍ፣ የሰው ልጅ ነፍስ ከፈጣሪዋ ጋራ ያላትን የማይቋረጥ ኅብረት የሚያሳይ የዕለት ተዕለት የነፍስ ስንቅ ነው። ከውጫዊው ዓለም ጫጫታና ጭንቀት ወጥተን፣ በልቡናችን ውስጥ ያለውን ዘለዓለማዊ ሰላም እንድንፈልግ ጥሪ የሚያቀርብና የእያንዳንዱን አንባቢ የዕለት ተዕለት ሕይወት ወደ ማያቋርጥ የጸሎት ተግባር ከፍ የሚያደርግ ድንቅ መንፈሳዊ መስታወት መሆኑን ገጾቹን ስንገልጥ ራሳችን እንመሰክራለን! የዚህን ተጓዥ አርኣያ በመከተል እኛም የጸሎተ ኢየሱስን መንፈሳዊ ጉዞ ዛሬውኑ ባለንበት ቦታና ኹናቴ እንድንጀምር ተጋብዘናል!

‘ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፥’

‘እኔ ኀጢአተኛውን ማረኝ!’

Mesfin Tekeste

@orthokiha

መጽሐፉን ያገኙታል

#አሳታሚና_አከፋፋይ

#አርጋኖን_መጻሕፍት_መደብር_5 ኪሎ_ቅድስት_ማርያም_ማኅበረ_ቅዱሳን_ሕንጻ_ግራውዱ_አጠገብ_0988888589_0925421700_ይደውሉ!